በአላህ ማመን

ዝግጅት፦
ሱልጣን ኸድር

© abuhuzeifa1431@gmail.com

በአላህ ማመን

በአላህ ማመን ማለት፦

- አላህ ሁሉንም ነገር የፈጠረና (ለፍጡራን የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በማቅረብ እና በማዘጋጀት) የሚንከባከብ፤አምላክ መሆኑን ማመን ማለት ነው።።
- ከርሱ በስተቀር አምልኮ የሚገባው አንድም አካል የሌለ፤መሆኑን ማመን ማለት ነው።።
- መልካም ስሞችና ባህሪያቶች ያሉት አምላክ መሆኑን ማመን ማለት ነው።።

የተውሒድ ክፍሎች

- ተውሒዱ አሩቡቢያህ
- ተውሒዱ አልኡሉሂያ
- ተውሒዱ አልአስማኢ ወሲፋት

ተውሒዱ አሩቡቢያህ

በሩቡቢያህ ማመን ማለት፦

አላህን በሰራዎቹ አንድ ማድረግ፡፡ይህም ማለት፤ መፍጠር፣ሲሳይን መስጠት፣ነገሮችን ማስተናበር፣ መግደል እና ህያው ማድረግ በመሳሰሉት ድርጊቶቹ አላህን ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው፡፡

ተውሒዱ አሩቡቢያህ

የሚከተሉትን ፅንሰ ሀሳቦች አካቶ ይይዛል።

- አላህ በመኖሩ ማመን
- ፍጥረታትን ለብቻው በማስገኘቱ ማመን
- ፍጥረተ ዓለሙን ብቻውን የተቆጣጠረ መሆኑን ማመን
- ፍጥረተ አለሙ ላይ አስተናባሪ መሆኑን ማመን

አላህ መኖሩን የሚያሳዩ መረጃዎች፦

አዕምሮአዊ ማስረጃዎች

ነገራት እራሳቸውን ሊያስገኙ አይችሉም።

ምክንያቱም ከመኖር በፊት አልነበሩምና

ያላስገኜ ሊገኙ አይችሉምና

ስለዚህም እነዚህን ያስገኘ አካል መኖሩ የግድነው

እርሱም አላህ ነው።

ተፈጥሮአዊ ማስረጃዎች

የሰው ልጆች በተፈጥሮዋቸው ያለብዙ ጥናትና ምርምር በቀላሉ ጌታ መኖሩን ይቀበላሉ።

ሰዎች ችግርና ጭንቅ ሲገጥማቸው ልባቸው ወደ ፈጣሪ ይቀጣጫል።

ተውሒዱ አልኡሉሂያ

ተውሒዱ አልኡሉሂያ ማለት፦

አላህን በአምልኮ አንድ ማድረግ ወይም መነጠል ማለት ነው።

ዒባዳ (አምልኮ)

ተግባሮች

ውስጣዊ

ውጫዊ

ንግግሮች

ውስጣዊ

ውጫዊ


አምልኮ (ዒባዳ)፡- ዒባዳ አላህ ለሚወዳቸው ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ንግግሮች እና ተግባሮች ሁሉ የተሰጠ ስያሜ ነው።

የላኢላህ ኢለላህ ትርጉም፦

ላኢላህ ኢለላህ
ማለት
ምን ማለት ነው?

ከአላህ በስተቀር በሀቅ አምልኮ
የሚገባው ማንም የለም ማለት ነው።

የ"ላ ኢላህ ኢለላህ" መስፈርቶች (ሸርጦች)፦



የዒባዳ ማዕዘናት፦

የዒባዳ ማዕዘናት ሦስት ናቸው።

- መሐባ (ውዴታ)
- ፍራቻ (ኸዉፍ)
- ተስፋ ማድረግ (ረጃዕ)

ተውሂድ አል አስማዕ ወስሲፋት፦

በቁርዓን እና ትክክለኛ በሆኑ የመልዕክተኛው ﷺ
ሐዲሶች ውስጥ የመጡትን የአላህ ስሞች እና ባህሪያት
ከማንም ስሞችና ባህሪያት ጋር ሳያመሳስሉ፣ ቃሉን
ሳያዛቡ፣ ትርጉማቸዉን ሳይለውጡ ወይም ሳያስተባብሉ
ለአላህ እንደሚገቡ በማመን ማፅደቅ ማለት ነው።።

አስማዕ ወስሲፋት ላይ የተፈጠሩ ስሕተቶች (ጠንቆች)፦

- አተዕጢል (ትርጉም አልባ ማድረግ)
  - ለምሳሌ፦ አላህ እጅየለውም ብሎ መካድ።
- ተምሲል (ማነጻጸር ወይም ማመሳሰል)
  - ለምሳሌ፦ የአላህን ﷻ እጅ ከሰው ልጅ እጅ ጋር ማመሳሰል፡፡
- ተሕሪፍ (የአንድን መረጃ ቃል ወይም ትርጉም ተቀባይነት ወደሌለው ትርጉም ማዞር)
  - ለምሳሌ፦ የአላህን ﷻ እጅ ችሎታው በሚል መተርጎም።
- ተክዪፍ (የመግለጫን አካኋን እንዴትነት ዝርዝር ማብራሪያ መስጠት)
  - ለምሳሌ፦ አላህ ﷻ በእንዲህ አይነት አካኋን ከዐርሹ ላይ ይገኛል ብሎ ገለጻ መስጠት፡፡

የአላህ ﷻ መገለጫዎች ከዘውታሪነት እንዲሁም “አዲስ” ክስተት ከመሆን አንፃር፡-

“ሲፋቱ ዛቲያህ” ይህም ማለት ‹‹ዘውታሪ የሆኑ መገለጫዎች››

‹‹ሲፋቱ ፊዕሊያህ›› ይህ ማለትሲሻ የሚተገብራቸው ሳይሻደግሞ የማይተገብራቸው መገለጫዎች

ለምሳሌ ፡- ዒልም (እውቀት) ፣ ቁድራ (መቻል) ወዘተ ..

ለምሳሌ፡”አልከላም” (ንግግር)፤ ለምድር ቅርቧ ወደሆነች ሰማይ መውረድ ..

በአላህ ስሞችና ባህሪያት ዙርያ ያሉ ጥቂት መርሆ

አስማኡ ወሲፋት

የአላህ ስሞች በቁጥር የተገደቡ አይደሉም

የአላህ ስሞችና መገለጫዎች በቁርአንና በሐዲስ የተገደቡ ናቸው።።

የአላህ ﷻ ስሞች ከሁሉም በተሻለ መልኩ እጅግ ውብ የሆኑ ስሞች ናቸው ።።

የአላህ ﷻ ስሞችና መገለጫዎች ትርጉማቸው የሚታወቅ ሲሆን ሁኔታቸው ወይም አኳኋናቸው ግን አይታወቅም።

በአላህ ስሞችና ባህሪያት አላህን ማምለክ

የአላህ ስሞችና ባሕሪያትን ትርጉማቸውን መገንዘብ።

የአላህ ስሞችና ባሕሪያት የሚያስፈርዷቸውን ተግባራት መፈፀም።

የአላህ ስሞችን ማላቅና ማወደስ።

በአላህ ስሞች እርሱን መለመን።

የአላህ ስሞችና ባህሪያት በአግባቡ የሚያምን ሰው የሚያገኛቸው ፋይዳዎች፦

1. አንድ አማኝ በዚህ እምነቱ የተነሳ የዱንያንና የአኺራን ተድላና ደስታን ይጐናፀፋል።።የሁለቱ ሀገር ስኬትና እድለኝነት የሚረጋገጠው በአላህ በማመን ብቻ ነው።።

2. አንድ አማኝ በጌታው ስሞችና ባህሪዎቹ የሚኖረው እምነት አላህን በሚገባ ለመፍራትና ትዕዛዙን ለመፈፀም ምክንያት ይሆነዋል።።

3. አንድ አማኝ በዚህ እምነቱ ሳቢያ የሁለቱ ሀገር የልብን መረጋጋት፣ የነፍስን እረፍት፣ ሰላምና መመራትን ይጐናፀፋል።።)

ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَطۡمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكۡرِ ٱللَّهِۗ أَلَا بِذِكۡرِ ٱللَّهِ تَطۡمَئِنُّ ٱلۡقُلُوبُ٢٨) [الرعد: 28]

የአላህ ስሞችና ባህሪያት በአግባቡ የሚያምን ሰው የሚያገኛቸው ፋይዳዎች፦

4 በመጪው ዓለም መልካም ምንዳ ማግኘት የሚችሉት በአላህ ላይ ያመኑ ሰዎች ብቻ ናቸው።።

5 ስራዎች ተስተካክለው ተቀባይነት የሚኖራቸው በአላህ ማመን ላይ የተገነቡ ከሆኑ ብቻ ነው።።

6 የአላህን ስሞችና ባህሪዎች በአግባቡ ማወቅ አላህ እንዲወደድ ያደርጋል።። ምክንያቱም የአላህ ስሞችና ባህሪዎች በሁሉም አቅጣጫዎች የተሟሉ ሲሆኑ ነፍስ ደግሞ ምሉዕን ነገር ትወዳለች።።

➢ የአላህ ውዴታ በልብ ውሰጥ ከፀና አካል ለመልካም ሰራ ታዛዥ ይሆንና ሰዎች የተፈጠሩለትን ዓላማ (ዒባዳ) ይተገብራሉ።

7

በአላህ ማመን አማኞች በቅርቢቷ አገር ለሚገጥሟቸው ማንኛውም መጥፎ ነገር ይሁን መልካም ነገሮች መጠጊያቸውና መሸሻቸው ነው።

8

የአላህን ውብ ስሞች በሚገባ ማወቅና መሸምደድ የእውቀቶች ቁንጮ ነው፡፡ማለትም እነሱን በሚገባ የሚረዳ እውቀትን ከመሰረቱ ይገነዘባል፡፡